የሰ/መ/ቁ. 26839

ኀዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ**

**ፍስሐ ወርቅነህ**

**ሐጎስ ወልዱ**

**ሒሩት መለሠ**

**ታፈሰ ይርጋ**

**አመልካች፡- ወ/ሮ አስካለ ለማ - ቀረቡ፡፡**

**ተጠሪ፡- ሣህለ ሚካኤል በዛብህ - ቀረቡ፡፡**

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በንብረት ክፍፍል ላይ ያደረጉት ክርክር ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ላይ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በ82 ካ.ሜ. ላይ የተሠራ ቪላ ቤት ከጋብቻ በፊት የተሰራ የግላቸው መሆኑንና ሌሎችን ንብረቶች ዘርዝረው በማቅረብ ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ደግሞ የግል ቤቴን ሸጬ ባገኘሁት ገንዘብ ቤቱን ከማኅበሩ ተረክበን አፍርሰን አሁን ያለውን ይዞት እንዲኖረው አድርገን ስለሰራነው የግሉ አይደለም፤ እዳው ከጋብቻ በኋላ ነው የተከፈለው እንዲሁም ከሌሎቹ ንብረቶቹ ውስጥ በውርስ ያገኘኋቸው የግል ንብረቶቼ ይገኙበታል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ከጋብቻ በኋላ ተሰሩ የተባሉት ስራዎች ተገምተው ብር 82,293 (ሰማኒያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት) ስለሆኑ የዚህን ዋጋ ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች ከፍለው ቤቱን ያስቀሩ በማለትና በሌሎቹም ንብረቶች የክፍፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡



ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ውሣኔን አጽንቶታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ግምት ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ሂደት እንደተረዳነው ተጠሪ ግምት ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የተወሰነው ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተገኘ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት ነው፡፡ በመሆኑም ክርክር የተነሳበት ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት ነው ወይስ የተጠሪ የግል ሃብት የሚለው ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 57 ያመለክታል፡፡ አንድ ንብረት ከግል  እና ከጋራ ሃብት ተቀላቅሎ የተገኘ ከሆነ ግን ንብረቱ የጋራ ወይም የግል ተብሎ እንደሚቆጠር የሕጉ ድንጋጌ በግልጽ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ድንጋጌውን ከአላማው አኳያ መተርጎም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከጋብቻ በፊት የነበረ ንብረት የጋራ እንዳይሆን የተፈለገበት ምክንያት ጋብቻ ንብረት ለማግኘት በሚል ሃሣብ ብቻ እንዳይቋቋምና እንዳይፈርስ ለመከላከል ሲባል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ምንም ንብረት ያልነበረው ሰው ንብረት ያለውን ሰው በማግባት ጋብቻ ሲፈርስ ያላፈራውን ንብረት የሚካፈልበት ሁኔታ ማመቻቸት ለፍትሕ እና ለሕሊና ተቃራኒ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ነገር ግን ለአንድ ንብረት መገኘት ተጋቢዎቹ ያደረጉት አስተዋጽኦ ተመርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ የግል ወይም የጋራ ሊባል ይገባል፡፡ ይህንንም ለመወሰን በንጽጽር ሲታይ አብዛኛው መዋጮ የተደረገው ከግል ነው ወይስ ከጋራ የሚለውን ከግምት ማስገባቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ንብረቱ በአብዛኛው ከጋራ ሃብት መዋጮ የተገኘ ከሆነና የግል

ንብረቱ ትንሽ ከሆነ ንብረቱ የጋራ ሆኖ መቆጠሩ ፍትሐዊ ይሆናል፡፡ የንብረቱ የተወሰነ ክፍል ከጋብቻ በፊት ተገኝቶ እንኳን ቢሆን አነስተኛ የሆነው ድርሻ ከግል ሃብት ከንብረቱ ላይ በመቀላቀሉ ብቻ ንብረቱ የግል እንዲሆን ማድረጉ ፍትሐዊ አይሆንም፡፡

ከዚህ ተነስተን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በእርግጥ ቤቱ የተጀመረው ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ቤቱ ተሠርቶ የተጠናቀቀው ከጋብቻ በኋላ እና ለቤቱ መስሪያ የተወሰደው ብድርም ከጋብቻ በኋላ መከፈሉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን ካረጋገጠ በኋላ ከጋብቻ በፊት የተሠራው ሥራ ምን ያሕል እንደሆነ ሳያጣራ እንዲሁም ከጋብቻ በኋላ የተሰራውንም ቢሆንም በገበያ ዋጋ ሳይሆን የመሃንዲስ ግምት ብቻ በማስቀረብ የዚህን ግምት ግማሽ ብቻ አመልካች ለተጠሪ ከፍለው እንዲያስቀሩ መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቤቱ ተጀምሮ ከማለቁ በፊት ጋብቻው እንደተፈፀመና የተጠናቀቀውም ከጋብቻ በኋላ መሆኑን፣ ለቤቱ መስሪያ የተወሰደው ብድርም ቢሆን ከጋብቻ በኋላ መከፈሉ አብዛኛው ወጪ ከጋራ ሃብት የወጣ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በእርግጥ በንብረቱ ላይ የተቀላቀለውን የግል ሃብት በተቀላቀለው መጠን የግሉ የሆነው ተጋቢ ሊወስድ ይገባል፡፡ ይህም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 86/1/ ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱ የተጀመረው ከጋብቻ በፊት በመሆኑ ብቻ ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 913 በግንቦት 29 ቀን 1996 ዓ.ም ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የሰጠው የውሣኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. የክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሃብት ነው፡፡
3. ከጋብቻ በፊት የተሠራው ሥራ ተገምቶ ግምቱ ለተጠሪ ይከፈል፡፡ ቤቱን ከተቻለ ግራ ቀኙ በዓይነት ይካፈሉ፣ ካልተቻለ አንዱ ለአንዱ የቤቱን የገበያ ዋጋ ግምት ከፍሎ ያስቀር፣ በዚህ የማይስማሙ ከሆነ ቤቱ ተገምቶ በሃራጅ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ እኩል ይካፈሉ፡፡



የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 26953

ኀዳር 13 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
መስፍን ዕቁበዮናስ
አብዱራሂም አህመድ
ሒሩት መለሠ
ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ - ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በአመልካች ጠያቂነት የቀረበ የሰበር ጉዳይ ነው፡፡

በወረዳው ፍ/ቤት  የአሁን መልስ ሰጭ ከሣሽ ነበሩ፡፡ ያቀረቡትም አቤቱታ ከመልስ ሰጪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን መነሻ በማድረግ የንብረት ክፍፍል ይደረግልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካችም በተከሳሽነት ቀርቦ ያካፍለኝ ስትል ከጠየቀችው ንብረት መካከል በእጁ የሚገኘው ቤት በወንድሜ ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ የእኔና የእርሷም አይደለም፡፡  እንዲያውም በእርሷ እጅ የጋራ ንብረት የሆነ ቤት የሚገኝ ስለሆነ ልታካፍለኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡